# እናት

የጐለደፈው ብዕሬ የአንደበቴ ቁንጽል ቃል
ውለታዋን ለመዘከር ለምስጋና መች ይበቃል?

ቢሆንም . . .
ልዩ ናት ምንጊዜም እናት
የማንነቴ ብርሃን የእኔነት ፋናዬ ብሥራት
የሕይወት ጸዳል እስትንፋስ የርኅራኄ ሠገነት
የፍቅር ሙዳይ ማኅደር የስብዕና መቀነት
የደግነት ምንጭ በረከት የተሰፋ ነጸብራቅ ጮራ
የሥነ ፍጥረት ለምለም መስክ የተመረጠች አዝመራ
የቅንነት መሠረት፣ የሐዘኔታ መፍለቂያ
የመሥዋዕትነት ማኅተም የመልካምነት መርቀቂያ

ናት ለእኔ እናት . . .
የፍጥረታት ዕጹብ አክሊል የትውልድ ምሰሶ ጽናት።
የሕይወትን ምጥ አምጣ ዓለምን በፍቅሯ ክባ
ችግር እንቅፋትን ችላ ትዕግስትን ተከናንባ
የጸጋ ምንጭ ናት እናት የደኅንነት መከለያ
የጽኑነት ምልክት የፍጥረታት መጠለያ።
እናት አገር ናት እምዬ የተሰፋ ረድኤት አለኝታ
የሰላም የክብር ዓርማ የእምነት አርአያ መከታ።

ታዲያ . . .
የቅጽል ብዛት ላይገልጻት
የጥበብ ብሩሽ ላይሥላት
ቅኔ፣ ስንኝ ቢቋጠር እሷነቷን ላይመጥናት
የምሁር ትንተና ስሌት የብዕር ቀለም ላይጠቅማት
ምን ልበላት?
ማን ላስብላት?
ከቶ በምን ልመስላት
በምን ቋንቋ ልሰይማት
ከቶ ምን ቃል ይበቃታል
የእናት እናትነቷን በምን ሰፍረው ይለኩታል?

አዎ . . . የጐለደፈው ብዕሬ የአንደበቴ ቁንጽል ቃል
ውለታዋን ለመዘከር ለምስጋና መች ይበቃል?!


ቴዎድሮስ አበበ
Washington, DC